# መሽ ደሞ አምባ ልውጣ!

አምባ ወጥቼ እኩለ-ሌት፥ ስለት ገብቼ በስሚ
ከርሞ ሰይጣን በሷ አስቶኝ፥ ልገላገል ከሕመሚ
ጠበሷ አፉፍ በጨረቃ፥ ደጋግሜ፥ ማሕሌት ቆሜ
ሆዴ ቃትቶ ባር ባር ብሎ፥ እርቃኔን ከሷ ታድሜ
ደጀ ሰላሚን በአራት እግር፥ ተንበርክኬ ተሳልሜ
በሥጋዬ እሚነደውን፥ በጸሎት ላቤ አጣጥሜ
እፎይ ብዬ አመስግኜ፥ ውዳሴዋን ደጋግሜ ....
ገና ከደጅዋ እልፍ ሳልል፥ ደሞ ይምጣ የቁም ሕልሜ?
ሌት በጥምቀቷ የነጣው፥ ነጋ፥ ደፈረሰ ደሜ።
ለሷ እንጂ ለኔ አልያዘልኝ፥ አዬ የስለት አታምጣ!
በውጣ ውረድ በጠበል፥ ባሣር ወዜ ቢገረጣ
ልክፍቷ እንደሁ አልለቀቀኝ፥ መሽ ደሞ አምባ ልውጣ!

፲፱፻፺፩ - ቢሾፍቱ